| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ግጥም ፤ "ከመቃብር ፡ በላይ" ፡ ዐምድ ። |
| ርእስ ፤ | "ቀኑም ፡ አመሻሸ ፥ ጀንበሯ ፡ ልትገባ ፤<br>ናፍቆት ፡ ሠቀቀኔ ፥ እምዬ ፡ ዐዲስ ፡ አባ ። " |
| ደራሲ ፤ | መኰንን ፡ ተክለ ፡ አረጋዊ ። (†) |
| ዕለት ፤ | 1970 ዎቹ ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቊ.2012-001 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | (ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያልታተመ ። ) |

---

# ከመቃብር ፡ በላይ ።

## ቀኑም ፡ አመሻሸ ፥ ጀንበሯ ፡ ልትገባ ፤
## ናፍቆት ፡ ሠቀቀኔ ፥ እምዬ ፡ ዐዲስ ፡ አባ ።

መኰንን ፡ ተክለ ፡ አረጋዊ [1] ።

---

የተወለድኹበት ፡ ባድማው ፣ መካኑ ፤
ያባቴም ፡ አበ ፡ ነፍስ ፡ አባ ፡ ብርሃኑ ፤
የዐይን ፡ አባቴ ፡ ደሞ ፡ ቱርክ ፡ ባሻ ፡ ሣህሉ ፤
የክርስትና ፡ አባቴ ፡ በላቸው ፡ ፍልፍሉ ፤
የጡት ፡ አባቴም ፡ አሻግሬ ፡ አካሉ ።
ባልንጀሬ ፡ ፍቅሬ ፥ ዐብሮ ፡ አደጌ ፡ ጓዴ ፥
ትኾን ፡ በላይ ፡ ኀይሉ ፡ ታሽመች ፡ አርምዴ ።
ቀኑም ፡ አመሻሸ ፥ ጀንበሯ ፡ ልትገባ ፤
ናፍቆት ፡ ሠቀቀኔ ፥ እምዬ ፡ ዐዲስ ፡ አባ ።

ዕትብቴ ፡ ያረፈበት ፥ መካበቢያችን ፥
ዳስ ፡ የተጣለበት ፡ ዐጥር ፡ ግቢያችን ።
ያባቴ ፡ ወዳጆች ፥
የጽዋ ፡ ወንድሞች ።
ዐቅፈው ፡ ያሳደጉኝ ፡ ዘመዶቻችን ፤
የቡሔ ፡ የሰጡኝ ፡ ወገኖቻችን ።
ቀኑም ፡ አመሻሸ ፥ ጀንበሯ ፡ ልትገባ ፤
ናፍቆት ፡ ሠቀቀኔ ፥ እምዬ ፡ ዐዲስ ፡ አባ ።

ፊደል ፡ ያስቈጠሩኝ ፡ አለቃ ፡ ብርሌ ፤
የሚያቈላምጡኝ ፡ አፈ ፡ መምህር ፡ ገድሌ ።
ቈንቋናዋ ፡ ዐቃቢት ፡ እማሆይ ፡ ይረፉ ፤
እጅግ ፡ መልካሙ ፡ ሰው ፡ ሊቀ ፡ ዲያቆን ፡ ዘርፉ ።
ንፉጉ ፡ መጨኔ ፥
ቈፍቋፋው ፡ ተገኔ ።
ዕቃ ፡ ቤት ፡ ጠባቂው ፡ ቍጡው ፡ አቶ ፡ ባንጃው ፤
የተዘለልኹበት ፡ መስኩና ፡ ማርገጃው ፤
ሰሜን ፡ ዐዲስ ፡ አባ ፥ ቀበና ፡ አባ ፡ ጐራው ።
ቀኑም ፡ አመሻሸ ፥ ጀንበሯ ፡ ልትገባ ፤
ናፍቆት ፡ ሠቀቀኔ ፥ እምዬ ፡ ዐዲስ ፡ አባ ።

ምስጢርን ፡ ዐውቄ ፥
ለምድን ፡ አጥልቄ ፥
ባለመርገፍ ፡ ጥላን ፡ ዘርግቼ ፥
ጧፍን ፡ አብርቼ ፥
ሥዕለ ፡ ማርያምን ፡ ይዤ ፥
ቃጭልን ፡ እየመታኹ ፡ ዐጅቤ ፡ ተጕዤ ፥
ታቦትን ፡ ያነገሥኹበት ፥
ቡራኬን ፡ የተቀበልኹበት ።
ሰበካና ፡ አጥቢያችን ፥
ዐምባው ፡ መንበራችን ።
ከብት ፡ የጠበቅኹበት ፡ ቍጥቋጦና ፡ ጥሻው ፥
ምንጩና ፡ ፏፏቴው ፥
አዟሪቱ ፡ ኩሬው ፥
መልካውና ፡ ዥማው ፥
እንግጫ ፣ ቄጠማው ፥
እንቧጮው ፣ አሓያው ፥
ጨሌውና ፡ አዠራው ፥
እምብልባዩ ፡ ወይራው ፥
ግራርና ፡ ዝግባው ፡
አጋሙና ፡ ቀጋው ፥
ምሽግ ፡ እደረቱ ፥ ቊልቋል ፡ መንፏቀቂያው ፥
ዶሮ ፡ ቤት ፡ ዐዘቅቱ ፥ የኳስ ፡ መጫወቻው ፥
ፈረስ ፡ መጋለቢያው ፥
ዐይኔ ፡ ሞሳ ፡ ሜዳው ፥
በርመጅ ፡ ሜዳ ፡ አፋፉ ፥ የሾላ ፡ መልቀሚያው ፥
ኰሽምና ፡ እንጆሪው ።

---

1 በ 1970 ዎቹ ፡ በሱዳን ፡ በረሓ ፡ በጠላት ፡ የተገደለ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የነጻነት ፡ ታጋይ ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ቡሔ ፡ የጨፈርንበት ፡
የሰጠንን ፡ አመስግነን ፣ የነሣንን ፡ የረገምንበት ።
ጅራፍ ፡ ያነጓንበት ፣ ጐባታው ፡ ዳገቱ ፣
ቀ፦ግ ፡ እሚገዙልኝ ፡ ኻዳዳ ፡ አታቱ ።
የተጋረፍንበት ፡ ሜዳው ፡ ሽንተረሩ ፣
ትዝ ፡ አለኝ ፣ ውል ፡ አለኝ ፡ ዐምባውና ፡ አገሩ ።
ቀኑም ፡ አመሻሽ ፣ ጀንበሯ ፡ ልትገባ ፤
ናፍቆት ፡ ሠቀቀኔ ፣ እምዬ ፡ ዐዲስ ፡ አባ ።

የእምዬ ፡ እንጐቻዋ ፣
መልካም ፡ ዐዋዜዋ ፣
ዝልል ፡ ወጥ ፡ ቋንጣው ፡ ጠጅና ፡ ጠላዋ ፣
የእኽል ፡ ወጥ ፡ አትክልቱ ፡ የሴት ፡ ባልትናዋ ።
ቄሎና ፡ ኀብስቷ ፣
ዳቦና ፡ ወተቷ ፣
ከኸሉም ፡ ከኸሉ ፡ ለእኔ ፡ ዐዛኝነቷ ።
አሳዳጊ ፡ እናቴ ፣ እማምዬ ፡ እንሰኔ ፣
ደጉ ፡ ባለቤቷ ፣ ነፍሱን ፡ ይማር ፡ ዐይኔ ።
እታለም ፡ እጅግ ፡ ሰው ፣ ተወዳጇ ፡ አክሥቴ ፤
ወርቅ ፡ ያንጥፉ ፡ ላንቺ ፣ ጡት ፡ አስጣይ ፡ እኅቴ ፤
ማሙዬ ፡ የምትለኝ ፣ እንኩዬ ፡ ኵራቴ ።
መራጫችን ፡ ወንዙ ፣ ትልቁ ፡ ቀበና ፤
ዋና ፡ አስተማሪያችን ፣ ሮቢ ፡ ጐበና ።
እኽል ፡ የሚደፍረው ፣ ጉደታ ፡ ጃውሳው ፤
ዐመለ ፡ መልካሙ ፣ አበበ ፡ ወላንሳው ።
አቶ ፡ ያደቴ ፡ ጣሊ ፣ እነእሜቴ ፡ ኩምባ ፤
ግንበኛው ፡ ገለቱ ፣ ልጃቸው ፡ ዲባባ ።
ቄሰ ፡ ገበዝ ፡ ተስፋ ፣ ያምሳ ፡ አለቃ ፡ ጉርሙ ፤
ወይዘሮ ፡ የሹም ፡ ነሽ ፣ አጋፋሪ ፡ ዓለሙ ።
ዳቦ ፡ የሚሼጡልን ፣ እማሆይ ፡ ሐደ ፡ አሸኩ ፤
ኩሶ ፡ የሚያመጡልን ፣ ትዝ ፡ የሚሉኝ ፡ ሚስኩ ።
ሱሪ ፡ የሚሰፉልኝ ፣ ኹነኛው ፡ ገላጋይ ፤
የርሳቸው ፡ ባልተቤት ፣ ለተ ፡ ብርሃን ፡ ዓባይ ።
ዳርሙላ ፡ አያ ፡ ኾቸር ፣ ወንድሙ ፡ አያ ፡ አንቀኞ ፤
እንኩዬ ፡ ደማሜ ፣ መልካሟ ፡ እናቴ ፡ አምቾ ።
ወተት ፡ የሚያጠጡ ፣ ጐምቱው ፡ አቶ ፡ አበቤ ፤
ክራር ፡ የሚቃኙት ፣ ቧልተኛው ፡ ድባቤ ።
ቀኑም ፡ አመሻሽ ፣ ጀንበሯ ፡ ልትገባ ፤
ናፍቆት ፡ ሠቀቀኔ ፣ እምዬ ፡ ዐዲስ ፡ አባ ።

ተማሪ ፡ ቤታችን ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፤
ሥርዐት ፡ አስከባሪው ፡ ኀይለ ፡ ማርያም ፡ ቢያዝን ።
ርእሰ ፡ መምህሩ ፣ የካናዳው ፡ ዘርፌል ፤
የስካውት ፡ አሠልጣኙ ፣ አቶ ፡ ሀርዲ ፡ ማክቤል ።
መምህር ፡ ተሰማና ፡ ቄስ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፤
መልአኩና ፡ ዐግዜ ፣ ልጅ ፡ ፈሪሳ ፡ ኦብሴ ።
የቅርብ ፡ ጓደኛዬ ፣ ዘለቀ ፡ ተገኔ ፤
መልካሙ ፡ መምህሬ ፣ አበበ ፡ ተጫኔ ።
የብስክሌት ፡ ተራ ፣ መገን ፡ ስድስት ፡ ኪሎ ፤
ጉልቱ ፡ ገበያ ፣ የአብሽሎ ፡ የቄሎ ።
የቀጨኔው ፡ ብዩ ፣ ኩራዬ ፡ ነጭናጫው ፤
ምትካቸው ፡ ነበር ፡ ለእኔ ፡ የሚቀርበው ፤
ሻይ ፡ የሚሼጡልን ፡ በርጋና ፡ ደላላው ።
ቀኑም ፡ አመሻሽ ፣ ጀንበሯ ፡ ልትገባ ፤
ናፍቆት ፡ ሠቀቀኔ ፣ እምዬ ፡ ዐዲስ ፡ አባ ።

በፈረንሳይ ፡ ድልድይ ፣ ፲ኛ ፡ ሻለቃው ፤
ከላይ ፡ ከዳገቱ ፣ ቀ፦ልቀ፦ል ፡ መዘቅዘቂያው ፤
በአቶ ፡ ዕርገቱ ፡ ሜዳ ፣ ቀበና ፡ መዝለቂያው ።
ከንግድ ፡ ርብርብቦሽ ፤
ከወረራ ፡ ምላሽ ።
አህያው ፡ ሲንጋጋ ፤
ጐበዙ ፡ ሴቷን ፡ ሲያቅፍ ፣ ሊስማት ፡ ሲጠጋ ።
የከንፈር ፡ ወዳጆች ፤
ለበቅ ፡ የሚመስሉ ፣ ቀዘባ ፡ ኰረዶች ፤
ወሲፍ ፡ የመሰሉ ፣ ሶማያ ፡ ጐበዞች ።
እንዲሁም ፡ በንግሡ ፣ በእየክብረ ፡ በዓሉ ፤
በቡድን ፡ በቡድም ፡ እየኰለኰሉ ።
ለጥምቀት ፡ ለመስቀል ፤
ከአባት ፡ በቄየልን ፣ በወረደ ፡ ባህል ።
በመንፈስ ፡ ትዝ ፡ አሉኝ ፤
ሲጫወቱ ፡ ታዩኝ ።
ቀኑም ፡ አመሻሽ ፣ ጀንበሯ ፡ ልትገባ ፤
ናፍቆት ፡ ሠቀቀኔ ፣ እምዬ ፡ ዐዲስ ፡ አባ ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፣ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ሽክላ ፡ የሚያበጁት ፡ አቶ ፡ ኹላ ፡ ካይጤ ፤
ድርብ ፡ ጥበብ ፡ ሠሪው ፡ ዶልዷላው ፡ አዝብጤ ፤
ጠላ ፡ የሚነግዱት ፥ ባልቴቷ ፡ በለጤ ።
ጥሩምባ ፡ የሚነፉት ፥ ወልቃባና ፡ ቡኔ ፤
ዝተት ፡ ቆብ ፡ የሰጡኝ ፥ ዐጪሩ ፡ አቶ ፡ አጕኔ ።
ዐናጢው ፡ አስገዶም ፥ ዘበኛው ፡ ቀቀባ ፤
ለሳኙ ፡ ደመቀ ፥ ወጥ ፡ ቤቱ ፡ ሰለባ ።
ቀኑም ፡ አመሻሽ ፥ ጀንበሯ ፡ ልትገባ ፤
ናፍቆት ፡ ሠቀቀኔ ፥ እምዬ ፡ ዐዲስ ፡ አባ ።

ቀበናን ፡ ለኑሮ ፥ እንጦጦን ፡ ለነፋስ ፤
ገዳም ፡ ሰፈርን ፡ ይዞ ፥ አሰለፈች ፡ ለዳንስ ።
የካን ፡ ለወተቱ ፥ ሾላን ፡ ለመዝናናት ፤
እሪ ፡ በከንቱ ፡ ለሁከት ፤
ቄራ ፡ ለጩኸት ።
ዐቧሬ ፣ ካዛንቺዝ ፥ ዑራኤል ፣ ፍል ፡ ውሃ ፤
ምርጫዬ ፡ እሱ ፡ ነበር ፥ መጠጤ ፡ በተሓ ።
ለገሐር ፡ ለባቡር ፥ በሩ ፡ መሿለኪያ ፤
ቂርቆስ ፡ አካባቢ ፥ ባራተኛ ፡ አቅራቢያ ።
አራት ፡ ኪሎ ፡ ግርግር ፥ የአቃዳ ፡ ጨዋታ ፤
ደርሶ ፡ ሽብ ፡ ረቡ ፥ ያ ፡ ኹሉ ፡ ጋጋታ ።
ሠራተኛ ፡ ሰፈር ፥ ወይ ፡ ዶሮ ፡ ማነቂያ ፤
ዕቍብ ፡ ለደረሰው ፡ ነበረ ፡ መታያ ።
ቀኑም ፡ አመሻሽ ፥ ጀንበሯ ፡ ልትገባ ፤
ናፍቆት ፡ ሠቀቀኔ ፥ እምዬ ፡ ዐዲስ ፡ አባ ።

ጃን ፡ ሜዳ ፡ አካባቢ ፥ ወይ ፡ ክቡር ፡ ዘበኛ ፤
እንዳልነበር ፡ ኾነ ፡ የኛ ፡ መገናኛ ።
በርበሬ ፡ በረንዳ ፥ እምዬ ፡ መርካቶ ፤
ጦም ፡ አያሳድሬ ፥ ምንም ፡ ቢኾን ፡ ከቶ ።
ሰንጋ ፡ ተራን ፡ ይዞ ፥ ባፋዛዥ ፡ ልደታ ፤
ቀጨኔን ፡ ለጥበብ ፥ ለሞንሚና ፡ ኩታ ።
ጌጃ ፡ ሰፈር ፡ ዕንብርቱ ፥ ጕለሌ ፡ ገፈርሳ ፤
ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ኳሮ ፥ እንዴት ፡ ነው ፡ መረሳ ፧
ቀኑም ፡ አመሻሽ ፥ ጀንበሯ ፡ ልትገባ ፤
ናፍቆት ፡ ሠቀቀኔ ፥ እምዬ ፡ ዐዲስ ፡ አባ ።

አራተኛ ፡ ጣቢያ ፥ ሰበሩ ፡ ቍጭራ ፤
የእነንቦ ፡ መንደር ፥ ማዶው ፡ አባ ፡ ቦራ ፤
ባሻገሩ ፡ ኰልፌ ፥ የማገዶ ፡ ተራ ፤
የጥናት ፡ መካኔ ፥ ቀበና ፡ ተራራ ፤
በዳንሴ ፡ ጋራ ፡ ሥር ፥ መንደሬ ፡ ጕራራ ፤
በዐሳብ ፡ ተሰደኻል ፡ አሉ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ።
የቦሌ ፡ ውብቱ ፥ መካኒሳ ፡ ወይኑ ፤
የአቃቂ ፡ ሽርሽር ፥ መናብቱ ፡ ደኑ ፤
ሥራቸው ፡ ተማሰ ፥ ኹሉም ፡ ዜሮ ፡ ኾኑ ።
ቀኑም ፡ አመሻሽ ፥ ጀንበሯ ፡ ልትገባ ፤
ናፍቆት ፡ ሠቀቀኔ ፥ እምዬ ፡ ዐዲስ ፡ አባ ።

አላምረውና ፡ እነኀይሌ ፡ ጦጤ ፤
ቤታቸው ፡ ሙዝ ፡ ተራ ፥ መንደራቸው ፡ ሲልጤ ።
እነእመት ፡ ጅፋሬ ፥ እነወፋ ፡ ደኀኔ ፤
የዓለሙ ፡ መስገጃ ፥ ገስማቸው ፡ ቀጨኔ ።
እነማሙዬና ፡ እነወልዳረጋይ ፤
አልተበሳ ፡ ይኾን ፧ ድቤያቸው ፡ አለ ፡ ወይ ፧
ቀኑም ፡ አመሻሽ ፥ ጀንበሯ ፡ ልትገባ ፤
ናፍቆት ፡ ሠቀቀኔ ፥ እምዬ ፡ ዐዲስ ፡ አባ ።

ከተማ ፡ የሚያደምቀው ፥ ወደልጋዙ ፡ ኹሉ ፤
ወፈፌው ፡ ጤነኛው ፥ ሞላው ፡ በጥቅሉ ።
እነአባ ፡ ቍረጣ ፥ ፤
እነአስረክብ ፡ አምጣ ።
እነአያ ፡ ቢኾነኝ ፤
እነወርደኽ ፡ ቈየኝ ።
እነአያ ፡ ቢቸግር ፤
እነወሬ ፡ ደርድር ፤
እነወልደኽ ፡ አጕር ፤
እነወግ ፡ ዐርቅ ፤
እነመንደር ፡ አድምቅ ፤
እነአሉባልታ ፡ ሰልቅ ፤
እነአንዣራሪ ፤
እነስመ ፡ ፈጣሪ ፤
እነእትዬ ፡ ላድርስ ፤


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

እነኹሉን ፡ ልቅመስ ፤

እነአናፍሴና ፡ እነአምታቴ ፤

እነዝራው ፡ አይታክቴ ፤

እነየዳስ ፡ ባላ ፤

እነነጥቆ ፡ በላ ።

እነአንዶልዱልና ፡ እነወልደ ፡ ሩፌ ፤

እነአዘጥዝጥና ፡ እነሽክም ፡ ትርፌ ።

እነየሺ ፡ ሐራምቤ ፤ እነአምሳለ ፡ ቡጊ ፤

እነገብሬ ፡ ገንጥል ፤ እነበሩን ፡ ዝጊ ፤

እነታዬ ፡ ሳምባ ፤

እነአልማዝ ፡ ሰለባ ፤

ግርማ ፡ ይለመጡ ፤ እነሥዩም ፡ ቈንጦ ፤

አበባ ፡ ዘረፉ ፤ እነሞላ ፡ በልጦ ፤

እነእብድ ፡ ይገዙ ፤ እነእትዬ ፡ ቦጌ ፤

እነጋሼ ፡ ቻቻ ፤ አብዬ ፡ ማሪንጌ ።

አቶ ፡ ውርባጎና ፡ እነቋንጤ ፡ ብሩ ፤

ይገሥግሡ ፡ ወዳንቺ ፤ አሉ ፡ ወይ ፡ ባገሩ ∴


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።